# እንዴት እኩል ይሙት!

የመከራ አባት፤የግፉ ባለቤት፤

የቀጠፈ ህይወት፤ስቃይን የዘራት፤

አገር የዘረፈ፤የከዳ የሸጣት፤

እርሱም ካንተ ጋራ፤እርሱም ጋንቺ ጋራ፤

እርሱም ከርሶ ጋራ፤እርሱም ከኔ ጋራ፤

እንደምን ይሆናል ከቶ በምን ምክንያት፤

ከኛ ጋራ አንዲት፤እንዴት እኩል ይሙት???

እኩልም አይኖርም፤

እኩልም አይሞትም፤

በቁምም መሞትም፤

አለ የሞት ሞትም፤

ለግፈኛ ሁሉ ከቶ አይቀርለትም።

ህይወትም አይደለም ሞትም መጨረሻ፤

የሰው ዘር ማክተሚያው ፍጻሜ መድረሻ።

እንዴት እኩል ይሙት እርሱም ከኛ ጋራ፤

እኩል እንደኖረ እኩል እንደሠራ።

ሂትለር ሙሶሎኒ፤

ጨጋኝ ገራዚያኒ፤

ነፍሰ ገዳይ ሁሉ፤

ዘራፊ በሙሉ፤

ማህደረ ተንኮል፤

እንደምን ይሞታል እርሱም ከኛ እኩል።

እንዴት እኩል ይሙት አፈር እንደሌላው፤

በቁሙ አለቱን ድንጋይ መሆን ሲያንሰው።

አንሞትም ይቅርብን ከርሱ እኩል እኛ፤

በእውነት የሚፈርድ በሌለበት ዳኛ፤

የሌላን አናውቅም እኛ ግን አንሞትም፤

ባልሠራነው ሥራ አኩል እንደማንም።

ይነገረን ዛሬ የሞት እኩልነት፤

ግፈኛን ከንጹህ ደብልቆ ማዳላት።

ለካስ፤ ለካስ፤ ለካስ፤ ጉዳዩ ሌላ ነው፤

መሞትም ህይወትም የአባት ውለታው፤

**በዚህና በዚያ ለካስ ሁለት ነው።**

በምድርም ህይወት፤

በአባትም መንግሥት፤

በምድርም መሞት፤

በሰማይም እሳት፤

ፍርድም ፍርድ ሆነች በመለኮት ስርአት።

ለዚህ ነው አንሞትም፤

ለኛ አይገባም፤

ብለን የሞገትነው፤

ሞትን ድል ልንነሳው።

ይኖራል በምድረ ይኖራል በሰማይ፤

ይሞታል በሞድረ ይሞታል በሰማይ፤

የሰው ዘር በሞላ ባባት ፍርድ ሲታይ።

ይቆጨን ነበረ ሁሉ በምድር ቢያልቅ፤

የዚሁ በዚሁ ሁሉ ቢጠናቀቅ፤

ነገሩ ሆነና ከሃሳብ የሚልቅ፤

መቀበል ብቻ ነው ጥያቄ-ሌለበት፤

**ዘመነ ማክተሚያ ዘመነ ምጽአት።**

እኛ አንሞትም ጭራሽ ምን ገዶን፤

ከነፍሰ ገዳዩ ከሚያስተካክልን።

አንሞትም እኛ ይቅርብን ይቅርብን፤

አዳይ በመሆኑ በሞትም አመጽን።

እኩልም አይኖርም፤

እኩልም አይሞትም፤

እንዴት እኩል ይሙት፤

ተቃውሞ መሟገት፤

በጣም ትክክል ነው አለ ዳግመኛ ሞት።

ይኸ የስጋ ሞት፤

ሽግግር ለበፊት፤

እውነተኛው መሞት፤

መኖርም በህይወት፤

የዘላለሙ ነው እርሱን መጣም ፍሩት።

አምሳ አመት እድሜ ሰባ ነው ቢበዛ፤

ማርጀት መጃጃቱ አይጥምም ቢንዛዛ፤

ጥርኝ አፍረ ሆኖ መቅረት እንደዋዛ፤

ላምሳ ሰባ ብሎ ዘላለምን ማጣት፤

አላዋቂነት ነው አልያም ሞኝነት;

ለዚህ ነው አንሞትም አሻፈረን ያልለው፤

አይንን ከገለጡ የሚታይ ብዙ ነው፤

ብዙ ነው!ብዙ ነው!ብዙ ነው! ብዙ ነው!!

ሞትም አይደለም ሞት፤

ህይወትም ህይወት፤

በጥብቅ ካሰተዋሉት፤

መርምረው ካገኙት።

አንሞትም እኛ ይቅርብን ይቅርብን፤

ካባታችን-ጋራ ሌላ ህይወት አለን፤

ያውም የዘላለም በጣም ደስ የሚለን፤

በህገ ስርአቱ በምነቱ ከሄድን።

ቢያንስ ተናግረለው ይውጣልን የውጣልን፤

ምን አገባውና እግዚአብሔር በሰጠን፤

ቢያሻን አንፈንዳ ቢያሻን እንታፈን፤

በአእምሮ ጓዳ ሁሉንም መዝነን፤

በሰው ግን አይሆንም በህግና በግድ፤

እርሱ ሊፈነድቅ ንጹህን ሊያግድ።

ፍርደ ገምድል ዳኛ፤

አንፈልግም እኛ!

ያባታችን እውነት፤

ያባታችን ህይወት፤

እርሱ ነው ዳኝለት፤

ፍርዱ ትክክል ናት፤

ሞትም ብትሆን ህይወት፤

ግልጽ ትርኩም አላት፤

በምድረ ከሆነ የውሀ ሽታ ናት።

የለም በዚች አለም፤ ፍርድም ቢሆን እውነት፤

ሁሉም እንደስራው ያድለዋል አባት፤

የዘለአለሙ ሁሉ ነው በደጁ፤

ማምለጥ አይቻልም ፈጽሞ ከእጁ ።

ፍአ

07 29 2012